# በዝማሬ ላይ ተዘወትረው የሚታዩ ዐቢይ ችግሮች



አዲስ አበባ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን
ስአገልጋዮችዋ ባዘጋጀችው ዐውደ ጥናት ላይ የቀረበ
ጥናታዊ ጽሑፍ
**ወርኀ ታኅሣሥ 2000 ዓ.ም**

ከተስፋዬ ሮበሌ









## ሒስ—እኮ ስምን?

***መዝሙር ዜማ የተቀላቀለብት የቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ወይም ስብከት ሲሆን፣ ዋነኛ ዐላማውም ቅዱሳንን ማነጽ እንዲሁም ከክርስቶስ የድነት ወንጌል ውጪ ያሉትን ሰዎች ወደ ትክክለኛው መሠረተ እምነት ማምጣት ነው:: ከተሞክሮአችን የምንማረውም ይህንኑ እውነት ነው:: በዝማሬ አገልግሎት ያልተባረከ በዝማሬ አገልግሎት ሐሴት የማያደርግ ክርስቲያን አለ ማለት በፍጹም የሚቻል አይመስለኝም:: ብዙ ሰዎች ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉት በመዝሙር አገልግሎት ውስጥ እንደ ሆነ መስክረዋል:: እርግጥ ነው መዝሙር እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣት ታላቅ ስጦታ ነው::***

***መዝሙርን ልዩ የሚያደርገው የዜማው ቃና ወይም መዝሙሩን የሚያጅቡት የሙዚቃ መሣሪያዎች የአደራደር ውበት ብቻ ሳይሆን ይዘቱና መልእክቱ ነው:: ይህ ጽሑፍ የሚያጠነጥነው በዜማው ወይም በሙዚቃ መሣሪያዎቹ ላይ ሳይሆን፣ በዝማሬው ይዘት ላይ ነው:: ይኸውም በሥነ ጽሑፋዊ (በቋንቋዊ) ይዘቱና በነገረ መለኮት ጭብጡ ላይ ነው::***

***የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት*** (High School) ***በነበርንበት ጊዜ*** "Common Mistakes in English" ***በመባል የሚታወቅ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አብዝተን እናነብ ነገር:: መጽሐፉ እንግሊዝኛ እናት ቋንቋቸው ያልሆኑ ሰዎች አዘወትረው የሚተላለፏቸውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ የሰዋስው ሕግጋት የትኞቹ እንደ ሆኑ የሚያስተምር መጽሐፍ ነው:: እኔ በግሌ ከመጽሐፉ ብዙ ጥቅም አግኝቻለሁ:: ልክ እንደዚህ መጽሐፍ ሁሉ፣ የዛሬው ትምህርት በዝማሬ ላይ ተዘወትረው የሚታዩ ዐቢይ ችግሮች የትኞቹ እንደ ሆኑ በወፍ በረር የምንቃኝበት*** ("Common Mistakes in Gospel Songs") ***ነው::***

***ቅዱሳት መጻሕፍት ሃይማኖታዊ ትምህርቶችንም ሆነ ክርስቲያናዊ ዝማሬዎችን ሁሉ ያለ አንዳች ማመንታት፣ በጥንቃቄ እንዲሁም በሙሉ ልብ እንድንመረምር አበክረው ቢያስገነዝቡም*** (***ዘዳግም*** 13÷1-5፤ 18÷20-22፤ ***ሐዋርያት ሥራ*** 17÷11፤ 2***ጴጥሮስ*** 2÷1፤ 3÷2፤ 1***ዮሐንስ*** 4÷1-2፤ ***ይሁዳ*** 17)፣ ***ይህን አምላካዊ ትእዛዝ ከሙሉ ልባችን ተግባራዊ እንዳናደርገው ልባችንን ሸብበው አፋችንን ለጉመው የሚይዙ ዘመን ያፈጁ በርካታ ጥያቄዎች አብረውን አሉ:: ለእነዚህ ጥያቄዎች*** (***ቢያንስ ዋና ዋና ለሚባሉት***) ***አጥጋቢ መልስ ማፈላለግ ካልቻልን፣ ቃለ እግዚአብሔር "መርምሩ" ሲል የሰጠንን ትእዛዝ ተግባራዊ ልናደርገው አንችልም:: ይህም ዐውደ ጥናት፣ "ለዘማርያን አሳውቃለሁ" የሚለው ዋነኛ ርእሰ ጉዳይ የተተለመለትን ግብ ሊመታ አይችልም:: ስለዚህ ከዚህ በመቀጠል ከበርካታ ሰዎች አፍ ተዘውትረው ለሚሰሙ ማነቄዎች መልስ ለመስጠት እንሞክራለሁ::***

## “በሌሎች ሰዎች መዝሙሮች ላይ ሒስ መሰንዘር ትክክል አይደለም!”

*“አንተ ማን ነህና ነው የሌላውን መዝሙር የምትተቸው?” የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፤ ተገቢ ጥያቄ ነው፤ ተገቢ መልስም ሊፈለግለት እንደሚገባም አምናለሁ። በሌሎች ሰዎች አስተምህሮም ሆነ ዝማሬ ላይ መፍረድ/ሒስ መሰንዘር ትክክል የማይሆንባቸው ሁለት መሠረታዊ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው:—* (1) *ርእሰ ነገሩን በጥልቀት ያልመረመረ ፍርድ ትክክል አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ፣ “ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ በመልክ አትፍረዱ”* (ዮሐንስ 7÷24) *የሚለው አነጋገሩ፣ ማናቸውንም ዐይነት ፍርዶችን የሚኰንን ሳይሆን፣ ፍርዳችን ምን ላይ ማነጣጠር/ ትኵረት ማድረግ እንደሚገባው የሚያስጠነቅቅ ነው። በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ትክክል አይደለም ያለው ፍርድ፣ ገጽታን በመመልከት ብቻ የሚካሄደውን ፍርድ ነው። ይኸውም ግልብ በሆነ ሁኔታ፣ የጕዳዩን ገጽ በመመልከት ብቻ ብቻ ርእሰ ነገሩን በጥልቀት ሳይመረምሩ የሚካሄደውን ፍርድ ማለቱ ነው።* (2) *ግብዝነት የሞላበት ፍርድ ትክክል አይደለም* (ማቴዎስ 7÷1-5፤ 23÷1-3)*። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ከጠማማ ልብ ተነሥተው የሚያደርጉትን ማናቸውም ነገር እግዚአብሔር ለበጎ ሊጠቀምበት ስለሚችል፣ ጠማማ ልብ ያላቸው ሰዎች እንኳ ሒስ ቢሰነዝሩብን በእነርሱ ማንነት ላይ ሆነን ሒሱን መመልከት ሳይሆን፣ ሒሱ በራሱ ትክክል ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጕዳይ ትኵረት ሰጥተን ልንመረምረው ይገባል* (ፊልጵስዩስ 1÷15-18)*። አንድ ሰው ምግባረ ብልሹ ነው ማለት ንግግሩም/ሒሱም የተበላሸ/ስሕተት ነው ማለት ላይሆን ይችላል። “የሰው ልጆች ፍጹማን አይደሉም፤ ስለዚህም ማናቸውንም ዐይነት ሒሶች መሰንዘር የለባቸውም” የሚሉ ሰዎች አሉ። ይህ ስሕተት ነው። አንድ ሰው እኔን፣ “በሌላው ላይ መፍረድህ ስሕተት ነው ቢለኝ”፣ እርሱ ራሱ በዚህ አነጋገሩ በእኔ ላይ እየፈረደ መሆኑ ሊታወቅ ይገባዋል* (*“በሌላው ላይ የምትፈርድ ማነህ?” እያለ እርሱ ራሱ በእኔ ላይ እየፈረደ ነውና*)*። ይህ እንዳለ ሆኖ ክርስቲያኖች ግን ራሳቸው ከሙሉ ልብ የተቀበሉትን እውነት ነው ሌሎች እንዲያከብሩት ማስተማር ወይም ሒስ መሰንዘር የሚገባቸው።*

*በሌሎች ሰዎች አስተምህሮ ወይም መዝሙር ላይ መፍረድ/ሒስ መሰንዘር ትክክል የሚሆነው፣ ሒሱ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ሲያደርግ ብቻ ነው። ዘማሪያን ነን ወይም ነቢያት ነን ወይም ደግሞ መምህራን ነን የሚሉ ሰዎች ትክክለኝነታቸው የሚረጋገጠው፣ አስተምህሮአቸው ከክርስቶስ ሐዋርያትና ነቢያት ትምህርት ጋር ተነጻጽሮ ትክክል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው* (*ሐዋርያት ሥራ* 17÷11፤ 2*ጴጥሮስ* 2÷1፤ 3÷2፤ 1*ዮሐንስ* 4÷1-2፤ *ይሁዳ* 17)*። የትምህርቱን ትክክለኝነትም ሆነ ስሕተት በትክክል ከተረዳን ደግሞ፣ ትክክለኛውን ትምህርት ትክክለኛ፣ የተሳሳተውን ደግሞ የተሳሳተ ማለት እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል* (*ሮሜ* 12÷2:9፤ 1*ቆሮንቶስ* 12÷10፤ 14÷29፤ 1*ተሰሎንቄ* 5÷19-22)*። ይህ ብቻ አይደለም በሥነ ምግባርም ሆነ* (*ማቴዎስ* 18÷15-18፤ 1*ቆሮንቶስ* 5÷9-13) *በአስተምህሮ* (*ሮሜ* 16÷17፤ *ገላትያ* 1÷6-9፤ 2*ጢሞቴዎስ* 3÷16-4÷4፤ *ቲቶ* 3÷10-11) *የሳቱትን ሰዎች ከስሕተታቸው እንዲመለሱ፣ ጊዜ ሰጥተን ማስተማርና መምከር ይኖርብናል። ከጥመታችን አንመለስም የሚሉ ከሆነ ግን ቢያስፈልግ ስማቸውን በመጥቀስ ደርጊታቸውንም ሆነ ትምህርታቸውን ማውገዝ እንደሚያስፈልግ ቃለ እግዚአብሔር ያስተምራል* (2*ጢሞቴዎስ* 2÷17፤ 2÷17)*። ከእንዲህ ዐይነቱ ሰውም ጋር ኅብረት እንዳናደረግ መጽሐፍ ቅዱስ በብርቱ ያስጠነቅቃል፣ “መከፋፈል የሚያመጣን ሰው አንድ ጊዜ ምከረው፤ ለሁለተኛ ጊዜ አስጠንቅቀው፤ ከዚያ ካለፈ ከእርሱ ጋር አንዳች ነገር አይኑርህ። እንዲህ ዐይነቱ ሰው የሳተና ኀጢአተኛ ነው፤ ራሱንም እንደሚኰንን ዕወቅ”* (*ቲቶ* 3÷10-11)።

## “እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ!”

*“ሰዎች ሁሉ በቃለ እግዚአብሔር ይመዘኑ” የሚለውን እውነት ታሳቢ በማድረግ፣ የአንዳንድ ግለሰቦችን ወይም ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እንዲሁም ዝማሬ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርገን ትምህርታቸውን፣ ምግባራቸውን ወይም ዝማሬአቸውን ስናሒስ ብዙ ሰዎች፣ “እግዚአብሔር*

በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ" የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በመጥቀስ፣ ሒሳችንን ከጅምሩ ያጣጥሉታል። እነዚህ ሰዎች ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በመጥቀስ ሊያስተላልፉ የፈለጉት መልእክት፣ "በእነዚህ ልዩ የእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ሒስ መሰንዘር የሚችለው ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው" የሚለውን ሐሳብ ነው። ይህ ሐሳብ ትክክል ነው ወይስ ትክክል አይደለም የሚለውን ጉዳይ ለመመርመር፣ "እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ" የሚሉትን ክፍሎች በቅርበት በመመርመር፣ የክፍሎቹን ትክክለኛ ትምህርት ከእነዚህ ሰዎች ሐሳብ ጋር በማነጻጸር ነው።

"እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ" የሚሉት ምንባባት የሚገኙት፣ በሚከተሉት ሁለት ክፍሎች ላይ (1ዜና 16÷22፤ መዝሙር 105÷6-14) ሲሆን፣ "የተቀቡ" የተባሉትም ሰዎች ርእሳን አበው ማለትም አብርሃም፣ ይስሐቅና ያቆብ ናቸው። የነገረ መለኮት ምሁራን እነዚህ ሰዎች "የተቀቡ" የተባሉበት ምክንያት፣ ቃለ እግዚአብሔር እንዲሁም የእግዚአብሔር ኪዳን በመጀመሪያ ወደ እስራኤል የመጣው በእነዚህ ሰዎች አማካይነት ስለሆነ ነው የሚል አስተያየት አላቸው። "የተቀቡ" የሚለው ቃል፣ "ነቢይ" የሚለውን ቃል እንደሚያሳይ ከዐውዱ በግልጽ መመልከት ቢቻልም፣ እነዚህ ሰዎች ግን ከነቢይ በላይ እንደ ሆኑ መገንዘብ ይኖርብናል፤ ምክንያቱም የእነርሱ ዝርያዎች የከነዓንን ምድር እንደሚገዟት እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋልና (መዝሙር 105÷11፤ ዘፍጥረት 17÷6:16፤ 35÷11)። ይሁን እንጂ ይህ አገላለጽ በመጽሐፍ ቅዱስ እምብዛም የተለመደ አይደለም (1ነገሥት 19÷16፤ ኢሳይያስ 61÷1)። ብሉይ ኪዳን "በእግዚአብሔር የተቀባ" የሚለውን ቃል የሚጠቀመው፣ (ቢያንዝ በአብዛኛው) ለእስራኤል ነገሥታት ነው (ለምሳሌ 1ሳሙኤል 2÷10:35፤ 16÷12-13፤ 2ሳሙኤል 1÷14:16፤ መዝሙር 2÷2፤ 89÷38:51፤ ዳንኤል 9÷25:26፤ 1ዜና 11÷3፤ 14÷8፤ 29÷22፤ ኢሳይያስ 45÷1)። ከእነዚህ ምንባባት በግልጽ የምንረዳው እውነት፣ በእግዚአብሔር የተቀቡ የተባሉት ሰዎች በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የነበራቸው ሰዎች ናቸው እንጂ መምህራን፣ ሰባኪያን፣ ወንጌላውያን ወዘተ አይደሉም። አንዳንድ ሰዎች በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ልዩ በሆነ ሁኔታ የሚጠቀምብኝ ልዩ ሰው ነኝ ስለሚሉ፣ በዚህ ማኅረግ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያቀርባሉ። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ያልተገነዘቡት መሠረታዊ ነጥብ፣ እግዚአብሔር እነዚህን የተቀቡ ሰዎች አትመርምሩአቸው ወይም አታሒሷቸው አላለም። ለምሳሌ በዘፍጥረት 20÷7 ላይ እግዚአብሔር ሣራን ለአብርሃም እንዲመልስ ለጌራራው ንጉሥ ለአቤሜሌክ ባስጠነቀቀው ጊዜ፣ እግዚአብሔር የአብርሃምን ነቢይነት መስክሮአል። ነገር ግን አብርሃም ነቢይ መሆኑ አቤሜሌክ የአብርሃምን ውሸት መርምሮ እንዳይረዳ አላገደውም (ቁጥር 9-10)። አንድ ሰው የእግዚአብሔር ነቢይ ነኝ እያለ፣ የተሳሳተ ዶክትሪን ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ትንቢት የሚያስተላልፍ ከሆነ፣ ይህን ነቢይ እንዳንቀበለው እንዲያውም እንድናወግዘው ቃለ እግዚአብሔር ያስተምረናል (ዘዳግም 13÷1-5፤ 18÷20-22)።

ሐዲስ ኪዳን፣ ክርስቲያኖች ሁሉ እንደ ተቀቡ በግልጽ ያስተምራል (2ቆሮንቶስ 1÷21)[1]። ስለዚህ ተቀብተናል በሚል ሒሳብ፣ ከቅዱሳት መጽሐፍት ትምህርት ጋር የሚቃረን ወይም በብሉያትና በሐዲሳት የሌለ ትምህርት የሚያስተምሩትን ሰዎች ትምህርት ያላንጻች ማቅማማት ወግድ ልንለው ያስፈልጋል (ገላትያ 1÷6-9)። በክርስቶስ ያገኘነውን ዐርነት የሚቃረን ነውና (1ዮሐንስ 2÷20:27)። ሐዲስ ኪዳን የሐሰት መምህራን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልከው እንደ ገቡ በግልጽ የሚያስተምርበት ሁኔታ (ሮሜ 16÷17፤ 1ጢሞቴዎስ 1÷3፤ ቲቶ 1÷11፤ 3÷10-11) "የተቀባሁ ሰው ነኝ"፣ "ማንም ትምህርቴን ወይም ትንቢቴን ወይም ደግሞ ዝማሬዬን ሊመረምር አይገባም" በማለት ከቃለ እግዚአብሔር ጋር የሚጋጭ ትምህርት ማስተማር ፈጽሞ ውጉዝ ነው።

[1] ይህን ርእሰ ጉዳይ በኋላ በስፋት እንመለከተዋለን።

## “መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው መዝሙሬ/ትምህርቴ አይገባውም፤ አልገባ ካለህ ጸልይ እንጂ አትፍረድ!”

*አንዳንድ ሰዎች፣ “እኔ የማስተምረው ትምህርት ወይም የምዘምረው መዝሙር መንፈሳዊነቱ እጅግ ጥልቅ ስለሆነ፣ የትምህርቴ ወይም የዝማሬዬ ጭብጥ አልገባ ካላችሁ፣ እግዚአብሔርን በጾምና ጸሎት ጠይቁት እንጂ፣ በትምህርቱ ላይ አትፍረዱ” ይላሉ—ከፈረድን ግን ቅሥፈት እንደሚጠብቀን። ይህ ዐይነቱ የአትመርምሩኝ ክልከላ ቢያንስ ሦስት መሠረታዊ ችግሮች አሉበት።* ***አንደኛ፤*** *ትምህርታቸው በመንፈሳዊ ይዘቱ የቱንም ያህል ጥልቅ ቢሆን፣ መሠረታዊ ከሚባሉት ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ጋር መጋጨት የለበትም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል እርስ በርሱ የሚቃረን አይደለምና። ስለዚህ ትምህርታቸው ዐበይት ከሚባሉት ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ጋር ምን ያህል ይጣጣማል የሚለው ጉዳይ የግድ ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ነው።* ***ሁለተኛ፤*** *ቃለ እግዚአብሔር “እጅግ ምስጢር” የሚለው፣ ለዘመናት ተሰውሮ የቆየውን የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው የመሆን ጉዳይ ነው። ይህ እውነት እንኳ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ይፋ አድርጐታል። ይህም ምስጢር ለዘመናት ተሰውሮ የነበረ፣ አሁን ግን ተገልጦ በይፋ የሚሰበክ መለኮታዊ እውነት ነው፣ “ይህም ቃል ከዘመናትና ከትውልዶች ተሰውሮ ምስጢር ሆኖ ቈይቶ ነበር፤ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል” (ቈላስይስ 1÷26፤ እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ሮሜ 11÷25፤ 16÷25፤ ኤፌሶን 1÷9፤ 3÷3:4:6:9፤ 5÷32፤ 6÷16፤ ቈላስይስ 1÷27፤ 2÷2፤ 4÷3፤ ራእይ 10÷7)። ስለዚህ በክርስቲያናዊ አስተምህሮ ውስጥ ይፋ ያልወጣ ወደ ፊት ይፋ የሚሆን ምስጢር አለ ማለት ስሕተት ነው*[2]*። የሐዲስ ኪዳን ቀኖና የተዘጋው፣ ለድነት የሚሆነን ማናቸውም ዐይነት ዕውቀት/እውነት በእግዚአብሔር ጸጋ ይፋ ስለተደረገልን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ መጽሐፍ ስለሆነ፣ እግዚአብሔር የቃሉን ትርጒም ለልቡናችን እንዲያበራ በፊቱ በትሕትና በመቅረብ ጸሎት ማድረስ እንደሚገባን ከሙሉ ልብ የምንቀበለው ጉዳይ ቢሆንም፣ የግለሰቦችን አስተምህሮ ለመረዳት ሱባኤ መግባት/አበክረን መጸለይ አይኖርብንም። መጸለያችን የግድ ሆኖ እንኳ ቢገኝ፣ ከጸሎቱ በኋላ ትምህርቱን መገምገም መፈቀድ ይኖርበታል። በጸሎትና በቃሉ የተጉ ወገኖች በትምህርቱ ላይ ፈጣን ግምገማ ቢያቀርቡ፣ “አልጸመም አልጸለየም” በሚል ብቻ ሒሳቸው ውድቅ ሊደረግ አይገባውም። ውድቅ መሆን ካለበት ውድቅ የሚሆነው የሁለቱም ወገን ማስረጃ (የተገምጋሚውም ሆነ የገምጋሚው) በሰከነ ሁኔታ ከተመረመረ በኋላ ነው።* ***ሦስተኛ፤*** *ቃለ እግዚአብሔር ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን ሁሉ እንድንፈትን ያስጠነቅቃል (ዘዳግም 13÷1-5፤ 18÷20-22፤ ሐዋርያት ሥራ 17÷11፤ 2ጴጥሮስ 2÷1፤ 3÷2፤ 1ዮሐንስ 4÷1-2፤ ይሁዳ 17)። ይህ ጉዳይ ደግሞ ሁሉን የምንፈትንበት ቃል (ሚዛን) እንደ ተሰጠን ታሳቢ ያደረገ ነው።*

## “ዋነኛው ነገር ‘ምን ታምናለህ’ የሚለው ሳይሆን ‘ምን ትሠራለህ’ የሚለው ጉዳይ ነው!”

*አንዳንድ ሰዎች፣ “ምግባር ከንድፈ ሐሳብ ይበልጣል” ይላሉ። ነገር ግን ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ምግባራችን የሚቃኘው/የሚገራው በአስተሳሰባችን/በአመለካከታችን መሆኑን በግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ነው። ሰዎች የሚተገብሩት (በተግባር ላይ የሚያውሉት) ትክክል ነው ብለው የሚያስቡትን ነገር እስከ ሆነ ድረስ፣ ምግባራችን ባለን ንድፈ ሐሳብ መመራቱ አይቀሬ ነው።*

---

*[2] “ምስጢረ ሥላሴ”፣ “ምስጢረ ሥጋዌ/ተሰግኦ”፣ “ምስጢረ ጥምቀት”፣ “ምስጢረ ቍርባን” እንዲሁም “ምስጢረ ጥምቀት” የምንላቸው ምስጢራት እስካሉ ድረስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምስጢር የለም ማለት ስሕተት ነው ሊባል ይችላል። ይህም ቢሆን የእነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች ምስጢርነት እንጂ የግለሰቦችን ትምህርት አይደለም። ምስጢር ቢባሉም እንኳ ቃለ እግዚአብሔር ስለእነዚህ ትምህርቶች የሚያስተምረው ትምህርት ስውር ነው ወይም ግልጽ አይደለም ማለት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለእነዚህ ትምህርቶች ዝርዝርና አጥጋቢ ትምህርት አለው። እነዚህ ትምህርቶች ምስጢር የተባሉበት ዋነኛ ምክንያት በሰብአውያን ተሞክሮ ላይ ሳይሆን፣ በእግዚብሔር ከሃሌ ኵሉነት ላይ መሠረት ስላደረጉ ብቻ ነው።*

በአንድ ርእስ ጉዳይ ላይ የተሳሳተ አስተምህሮ ያለው ሰው፣ በርእሰ ጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ሥራ ሊሠራ እንደማይችለው ሁሉ (ካልተሳሳተ በስተቀር)፣ ዶክትሪንም ሰዎች ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ክርስቶስ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ፣ ስለ ድነት፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ሰው፣ ስለ ኀጢአት ወዘተ ያላቸውን አመለካከት/አስተሳሰብ የሚወስን/የሚቀርጽ ጉዳይ ነው።

ይህ ማለት ግን ምግባራችን ዘወትር የሚመራው ትክክል ነው ብለን ባመንበት አስተሳሳብ ነው ማለት አይደለም። አንድ ሰው ውሸትን መናገር ስሕተት መሆኑን እያወቀ፣ ሽምጥጥ አድርጎ ሊዋሽ ይችላል። ለዚህም ነው፣ "ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው" የሚባለው (ያዕቆብ 2÷17)። ቤተ ክርስቲያን የተሳሳተ ትምህርት የሚከተለውን ብቻ ሳይሆን (ሮሜ 16÷17፤ 2ዮሐንስ 9-11፤ ኤፌሶን 4÷12-13)፣ በምግባረ ብልሹ የሆነውንም ሰው ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት ታገላለች (ማቴዎስ 18÷15-18፤ 1ቆሮንቶስ 5÷9-13)። ቤተ ክርስቲያን የተበላሸ ምግባር የለውን ሰው ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት ስላገለለችው፣ ግለሰቡ የዘላለምን ሕይወት አያገኝም ማለት ግን አይደለም። ነገር ግን ግለሰቡ በእኩይ ምግባሩ ተጸጽቶ ንስሓ እንዲገባ፣ በመጥፎ ምግባሩ ቤተ ክርስቲያንን እንዳያውክ እንዲሁም ሌሎች ክርስቲያኖች የግለሰቡን መጥፎ አካሄድ እንዳይከተሉ ለማስጠንቀቅ (እኩይነቱን በሌሎች ላይ እንዳያስተላልፍ) በሚል ብቻ ነው። በአጠቃላይ ዶክትሪን የሰዎችን ምግባርና እምነት የሚወስን መሠረታዊ ነጥብ ነው።

ስለምንኖርባት ዓለምም ሆነ ስለራሳችን ማንነት እንዲሁም ስለእግዚአብሔር ማንናትና ሥራ ያለን አመለካከት/ግንዛቤ የሚቀረጽው ባለን ዶክትሪን ነው። ያለ ዶክትሪን ትክክልኛና ውጤታማ ሕይወት መኖር አንችልም (ማቴዎስ 22÷23-33፤ ሮሜ 12÷3፤ 2ጢሞቴዎስ 4÷3-4)። ትክክለኛው ዶክትሪን ወደ ስሕተትና ወደ ጥፋት የሚወስደውን መንገድ እንዳንከተል አቅጣጫ ይጠቁመናል (1ጢሞቴዎስ 4÷1-6፤ 2ጢሞቴዎስ 2÷18፤ ቲቶ 1÷11)። ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን በምን መልኩ ማገልገል እንዳለብን ያስተምረናል (ኤፌሶን 4÷11-12)። በአንጻሩ የተሳሳተ ዶክትሪን ደግሞ ከዚህ ተቃራኒውን መንገድ እንድንከተል ያደርገናል። ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነቷን ለአገልጋዮችዋ በተለይም ደግሞ ለመምህራኖቿና ለዘማሪዎቿ በሚገባ ማስተማር ይኖርባታል። ሰው አስተሳሰብና አኗኗር እውነት ነው ብሎ ከተቀበለው መሠረተ እምነት የሚመነጭ ጉዳይ ነውና።

# የመዝሙሮቻችን ነገረ መለኮታዊና ሥነ ጽሑፋዊ ሕጸጾች

ከዚህ በመቀጠል በመዝሙር አገልግሎት ላይ ተዘውትረው የሚታዩትን ችግሮች በሁለት ከፍለን በዳሰሳ መልክ እንቃኛቸዋለን። ይኸውም ሥነ ጽሑፋዊ ስሕተቶችና ነገረ መለኮታዊ ስሕተቶች ናቸው።

# ሥነ ጽሑፋዊ/ቋንቋዊ ሕጸጾች

መጻሕፍቶች አቃጥሰው፣
አማልክቶች ሰባብረው፣

- በመዝሙሮቻችን ላይ ተዘውትረው የሚታዩ ችግሮች ነጠላ ቍጥርን ወደ ብዙ ቍጥር የምናረባበት መንገድ ነው። አማርኛ በርካታ ቃላትን ከግእዝ ቋንቋ ወስዶአል። ስለዚህ የግእዝ ቃላትን የምናረባው የአማርኛ ቃላትን በምናረባበት መንገድ አይደለም።

  አንድን የአማርኛ ቃል ወደ ብዙ የምንቀይረው በቃሉ ላይ "ኦች" "ዎች" የሚለውን ባዕድ መድረሻ በቃሉ ላይ በበጣል ነው። ለምሳሌ ፈረስ—ፈረሶች፣ ሰው—ሰዎች ፣ ላም—ላሞች፣ ተራራ—ተራሮች፣ በግ—በጎች፣ መኪና—መኪኖች። እንደ ብላታ መርስዔ ሐዘን ወልደ ቂርቆስ መጽሐፍ የአማርኛ አረባቦች የራሳቸው የሆነ ሕግ አላቸው። ይኸውም (1) መድረሻው ራብዕ

*ወይም ሳድስ የሆነ ቃል የመጨረሻ ፊደሉን ሳብዕ አድርጎ "ች" ሲጨመርበት ብዙ ይሆናል። ምሳሌ ጌታ—ጌቶች፣ ሰው—ሰዎች፣ ተራራ—ተራሮች እንደ ማለት ነው* (2) *መድረሻው ሳብዕ የሆነ ቃል ግን የመጨረሻ ፊደሉ ሳይለወጥ ች ይጨመርበትና ብዙ ይሆናል። ምሳሌ በቅሎ—በቅሎች፣ መሰንቆ—መሰንቆች እንደ ማለት ነው።* (3) *መድረሻው ካብዕ፣ ሣልስ፣ ሃምስ የሆነ ቃል መጨረሻ ፊደሉ ሳይለወጥ ዎች ይጨመርበትና ብዙ ይሆናል። ምሳሌ ክፉ—ክፉዎች፣ ፏታውራሪ—ፊታውራሪዎች፣ ገበሬ—ገበሬዎች።*

*ይህ እንዳለ ሆኖ ይህንን ሕግ ተከትለን ብናረባቸው ጣዕም ያማይሰጡና የተሳሳተ ትርጒም የሚያስከትሉ ቃላት አሉ በዚህ ጊዜ ሕጉን በመጣስ አማረጭ ሊሆኑ የሚችሉ የአረባብ መንገዶችን መከተል የግድ ይሆናል። ይህን የአረባብ መንገድ የማይከተሉ አንዳንድ የቋንቋ ሊቃውንት አሉ። እንደነዚህ ደግሞ፣* (1) *በሳድስ የሚደርሱትን መጨረሻቸውን ሳብዕ አድርጎ "ች" መጨመር፣* (2) *ለተቀሩት ግን በሙሉ "ዎች" የሚለውን ቅጥያ ያለምንም ለውጥ መጨመር ነው።*

*ከግእዝ የመጡትን ቃላት የምናረባበት መንገድ የራሱን የግእዝ ቋንቋ ሰዋስውን የተከተለ መሆን አለበት። ለምሳሌ ካህን—ካህናት፣ ጳጳስ—ጳጳሳት፣ ቃል—ቃላት፣ መነኩሴ—መነኮሳት፣ ሐዋርያ—ሐዋርያት፣ ንጉሥ—ነገሥታት፣ ነቢይ—ነቢያት፣ መጽሐፍ—መጻሕፍት፣ መምህር—መምህራት፣ መስፍን—መሳፍንት፣ ደብር—አደባራት፣ ቄስ—ቀሳውስት፣ መልአክ—መላእክት፣ ሊቅ—ሊቃውንት፣ ምሁር—ምሁራን፣ ጠቢብ—ጠቢባን፣ ቤት—አብያት፣ አገር—አጉር፣ ርእስ—አርእስት፣ ሕዝብ—አሕዛብ፣ ዐምድ—አዕማድ፣ ገዳም—ገዳማት፣ ድንግል—ደናግል፣ አንቀጽ—አናቅጽ፣ አንበሳ—አናብስት፣ ማኅበር—ማኅበራት፣ ዘማሪ—ዘማርያን።*

*ብዙ ዘማርያን፣ ነገሥታት፣ ነቢያት መጻሕፍት ዘማርያን የሚሉትን የብዙ ቊጥር የሚያመለክቱ የግእዝ ቃላት ነጠላ ቃል አድርገው ስለሚወስዷቸው በአማርኛ "ዎች" በመጨመር ሊያረቧቸው ይሞክራሉ። ይህ ጸያፍ አረባብ ነው። ይህ በብርካታ መዝሙሮች ላይ በጒልሕ የሚታይ ችግር ስለሆነ ሊስተካከል ይገባዋል።*

መንፈሱን ስቀቀብኝ

- *መንፈሱን ሰጠኝ፣ ለገሰኝ፣ ቸረኝ፣ አደለኝ፣ አቀበለኝ፣ ሸለመኝ፣ አበረከተልኝ፣ ከተባለ እንጂ፣ መንፈሱን ለቀቀብኝ አይባልም። ለቀቀብኝ አዎንታዊ ትርጒም ሳይሆን አሉታዊ ትርጒም ስላለው ነው። ለምሳሌ "ውሻውን ለቀቀብኝ" ከተባለ ውሻው እንዳይበላኝ ሊይዝልኝ ሲገባ ውሻውን ለቁ አስነከሰኝ ማለት ነው።*

ፍቅሩ ብሶበታል

- *ከላይ እንደ ተመለከትነው ሁሉ ብሶበታል የሚለው ቃል አሉታዊ ትርጒም ያለው ነው። ፍቅሩ ጨምሮአል፣ በርትቶአል፣ አድኋል፣ ጒልብቶአል፣ ወዘተ እንጂ ብሶበታል አይባልም። ችግሩ <u>ብሶበታል</u>፣ በሽታው <u>ጠንቶበታል</u>፣ ረሀቡ <u>ከፍቶአል</u>፣ ሲባል ብሶበታል፣ ጠንቶበታል፣ ከፍቶበታል ወዘተ የሚሉት ቃላት አሉታዊ ትርጒም ያላቸው ናቸው። ስለዚህ ፍቅር እና ብሶበታል ወይም ጠንቶበታል የሚሉት ቃላት አብረው የሚሄዱ አይደሉም። ምናልባትም በውስጠ ወይራ ምፀታዊ ትርጒም ያዘሉ ስለሚመስል የአማርኛ ዐዋቂዎች የመልእክቱን ተቃራኒ ትርጒም ለማስተላለፍ ተፈልጎ ነው ወደሚል ድምዳሜ ሊወስዳቸው ይችላል።*

ምክንያት ፈልጌ ሳመስግን እንጂ፣
ሰበብ ፈልጌ ልዘምር እንጂ፣

- "ሰበብ *ፈልጎ ደበደበኝ" ሲባል፣ ለመደብደብ የሚያበቃ ምክንያት ስለተገኘብኝ ሳይሆን፣ ሊደበድበኝ ስለቈረጠ/ስለፈለገ የማያስደበድበኝን ምክንያት እንደሚያስደበድበኝ አድርጎ በማቅረብ ደበደበኝ ማለት ነው። እግዚአብሔር ያደረገው ነገር ብዙ እያለ እንዴት ሰበብ እንፈልጋለን። ሰበብ ደግሞ አሉታዊ እንድምታ ያለው ቃል መሆኑን ልብ ይሏል። እግዚአብሔርን የምናመሰግነው ምክንያት ፈላልገን ሳይሆን ለማመስገን የሚያበቃ ትልልቅ ምክንያቶች ስላሉን*

*ነው። "ፈላልጌ" የሚለውም ቃል በጭንቅ በአሳር ተፈልጎ ለተገኘ ነገር እንጂ ላፈጠጠ እውነት እንዲያ አይባልም።*

o *በአጠቃላይ ዘማርያን የአንድን ቃል አረባብ በሚገባ ሊያውቁ ወይም ቃሉ አዎንታዊ ትርጒም አለው ወይስ አሉታዊ የሚለውን ጒዳይ በትክክል ሊያጠኑ ይገባቸዋል።*

# ነገረ መለኮታዊና ሕጸጾች

## *ትልቅነቱ እንዳይታወቅ ያደርገዋልን?*

አወቅሁ ብዬ ደምድሜ ሳበቃ፣
ማለዳ ማለዳ አንተ አዲስ ነህ ለካ፣
እንደተሳንትናው ከቶ አይደለህም፣
አንተ አትለመድም ዛሬም አዲስ ነህ፣

የማውቀን ልናገር ብሞክር፣
በየዕለቱ አዲስ ነህ እግዚአብሔር

*የሌላው ዘማሪ መዝሙር ደግሞ እንዲህ ይላል፣*

ብዙዎች ዐውቀናል እንዳሉ፣
በራሳቸው አእምሮ እንደ ሳሉ፣
አንተ ግን እንደዚያ አይደለህም፣
ትልቅ ነህ ማንም አያውቅህም።

*በእርግጥ እግዚአብሔር ትልቅ ነው። እንኳን እግዚአብሔርን፣ ዕልቀ-ኅ መሳፍርት የሌለውን ፍጥረተ ዓለም እንኳ ዐውቆ ለመዝለቅ አይቻልም። ነገር ግን ጽንፈ ዓለም ከአእምሮ በላይ ነው ወይም እግዚብሔር ከአእምሮ በላይ ነው ማለት፣ ስለ ፍጥረቱም ሆነ ስለ እግዚብሔር አንዳች የሚታወቅ ነገር የለም ማለት አይደለም። ክርስትና እግዚአብሔር በልዩ መገለጥም ሆነ በአጠቃላይ መገለጥ ራሱን ይፋ አድርጓል የሚል እምነት እስካለው ድረስ፣ እግዚአብሔር አይታወቅም ብሎ ማሰብ ስሕተት ነው። እግዚአብሔር አይታወቅም የሚሉ ሰዎች ያለመታወቁን እንዴት ሊያውቁ ቻሉ? እለመታወቁን ማወቃቸው ራሱ ዕውቀት ነው። በርግጥ እግዚአብሔር ምጡቅ አምላክ ስለሆነ ትንሿ አእምሮአችን ሊጨብጠውም ሆነ ፈጽሞና ጨልጦ ሊረዳው በፍጹም አይችልም። ይህ ማለት ግን በተወሰነ ደረጃም እንኳ ቢሆን ስለ እግዚአብሔር አናውቅም ማለት ትክክል አይደለም። "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ ዕቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው" (ዮሐንስ 1÷18) የሚለው ክፍል በተወሰነ ደረጃም እንኳ ቢሆን ስለ እግዚአብሔር ዕውቀት እንዳገኘን የሚስተምር ነው። የእግዚብሔርን ሁሉን ዐዋቂነት ለመግለጽ ሲባል፣ ስለ እርሱ አንዳች ዕውቀት እንደ ሌለን አድርጎ ማቅረብ ትክክል አይደለም።*

## *ኩሲ ለዳዊት ወይስ ዳዊት ለሳኦል?*

ዳዊት ዕፍል ገዳይ ሳኦል ግን ሺህ ብቻ፣
አያስ ቢዘፍኑ እሱ የሰው አቻ፣
ልብህ ቅር አይበለው ክፉ አትመኝለት፣
ይሁን እንዳሰኘው ቀን እስኪወጣለት።

*ይህ ግጥም መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትረካ አዛብቶ አቅርቦአል። ዘማርያን ታሪካዊ ክሥተቶችን ቃለ እግዚአብሔር በሚያስተምረው መንገድ መቅረብ አለባቸው።*

እርሱ እግዚአብሔር ነውና፣
ደስ የሚያሰኘውን ያድርግ አሜን ያድርግ።

*እርግጥ እግዚአብሔር ደስ የሚያሰኘውን እንዲያደርግ መሻት ተገቢ ነው። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ፣ "እርሱ እግዚአብሔር ነውና ደስ የሚያሰኘውን ያድርግ ያለው" ካህኑ ዔሊ ልጆችህን ቅጣ፣ ምከር፣ ገሥጽ የሚል ምክር ሲቀርብለት ልጆቹን ከመምከር ይልቅ በክፉ ድርጊታቸው እንዲቀጥሉ በሚፈቅድ መልኩ የተናገረው የስንፍና ንግግር ነው። በዚህም ንግግሩ እግዚአብሔር፣ "ከእኔ ይልቅ ልጆችህን አስበልጠሃል ብሎ ሲገሥጸው" እንመለከታለን። ማንኛውም ዐይነት አነጋገር መታየት ያለበት ንግግሩ በቀረበበት ዐውድ ትርጉም ስለሆነ፣ ንግግሮቹን ከዐውዳቸው አላቀን ለመተርጐም መሞከር የለብንም። ለማድረግ ብንሞክር እንኳ በአድማጮቻችን ጆሮ ውስጥ የሚያቃጭለው ንግግሩ የቀረበበት ዐውድ ስለሆነ ለማስተላለፍ የተፈለገው መልእክት በትክክል እንዳይደርስ መሰናክል ይሆንብናል።*

### *በርግጥ እግዚአብሔር ያዳላል?*

ስእኔ ግን እግዚአብሔር ያዳላል

*የእግዚብሔርን ለጋስነት ለመግለጽ፣ አድሎ አድራጊ አድርጎ ማቅረብ ስሕተት ነው። የዚህ ዝማሬ አድማጮች እንደ ዘማሪው ጮቤ የረገጡ፣ በእግዚአብሔር ባለውለታነት የተደሰቱ ቢያንስ ያሉበት ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቸርነት እንዳያጣጥሙ እክል ሆኖባቸው ሊሆን ይችላል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ላለ ሰው ይህ መዝሙር ከማነጽ ይልቅ የአፍራሽነት ሥራ ይሠራል። ዘማሪው እግዚአብሔር ያዳላል ለማለት የዳዳው የእግዚአብሔር ቸርነት ልቆ ታይቶት እንደ ሆነ እሙን ቢሆንም፣ ማዳላት ግን የእግዚአብሔር ባሕርይ ስላልሆነ አንዱን የእግዚአብሔር ባሕርይ ማለትም ቸርነቱን ለማድመቅ ሲባል እግዚአብሔርን ፍርደ ገምድል አድርጎ ማቅረብ ስሕተት ነው።*

### *ከክፍሉ ይህን ዐይነቱን ትምህርት መማር እንችላለንን?*

ጻድቅ ሲራብ፣ ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም፣

*ይህን ንግግር የተናገረው ንጉሥ ዳዊት ነው። እርሱ አላየሁም ካለ እኛም አናይም ማለት አይደለም። እንዲያውም ይህን መዝሙር የዘመረው የሶሎ ዘማሪ ጌታን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ከተቀበለ በኋላ ብዙ ታርዞ፣ ተርቦና ተጠምቶ እንዳለፈ መስክሮአል። ብዙዎቻችንም ክርስቲያን ከሆን በኋላም እንኳ በዚህ ሁኔታ ውስጥ አልፈናል። ዳዊት አላየሁም ስላለ እኛም ከእርሱ ጋር ተደርበን አላየንም ማለታችን ምክንያቱ ምንድን ነው። ንጉሥ ዳዊት ይህን ንግግር የተናገረው ለእስራኤል ወርቃማ ዘመን በተባለበት የታሪክ ወቅት ነው። በዚህን የታሪክ ወቅት ጻድቅ የተባለችው እስራኤል ተርባ አለመታየቷ ተገቢ ነው። በሌላ የታሪክ ጊዜ ደግሞ በሰማርያ ምድር እንደ ታየው ዐይነት አሠቃቂ ራብ ሕዝበ እስራኤልን አጥፍቶ ነበር። ዳዊት እኔ አላየሁም ስላለ እኛም እርሱን ተከትለን እኛም አላየንም ማለት የለብንም፤ በቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ የእርሱ ንግግር ጊዜ የማይሽረው እውነታ* (All Time Principle) *አይደለምና። ምንጨታዊ ምንባባትን* (*አስተምህሮን*) *ከመስተጋብራዊ* (*ከታሪክ*) *ምንባባት መለየት አለብን።*

### *እውነታው እንደዚያ ነውን?*

አስገረመኝ አስደነቀኝ፣
በጠላቴ ላይ ጌታ አደረገኝ

*የፍጥረት ሁሉ ጌታ፣ አምላካችን እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሱባኤ ስንገባ፣ ጾም ጸሎት ስናበዛ፣ ቅድስና ሲሰምርልን ወይም ስኬት ሲበዛልን እግዚአብሔር ጌትነቱን ወደኛ ያስተላለፈ ሊመስለን ይችላል። ነገር ግን ሰውና ሰው ብቻ ነን፤ ከዚህም አንጨምር ከዚህም አንቀንስ። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ሰዎች የአምላክነት ባሕርይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቈነጠረላቸው የሚል ትምህርት አላቸው*[3]*። "እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በአምሳሉ ፈጠረው" ወይም "የመለኮት*

---

[3] *የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን ወይም የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አራማጆች።*

*ባሕርይ ተካፋዮች ናችሁ" ወይም "ደግሞ ክርስቶስን ለመምሰል ተጠርታችኋል" ማለት አምላክ ናችሁ/የአምላክነት ባሕርይ አለባችሁ ማለት አይደለም*[4]::

አበቃለት ሲል ጠላት ሲፎክር፣
ስሳልገባው ቅባቴ እንደሚጨምር፣

*ይህ ዐይነቱ መዝሙር ቅባትን/መቀባትን አስመልክቶ አንዳንድ ሰባኪያንና መምህራን ካስተማሩት የተሳሳተ ትምህርት የመነጨ ትምህርት መሆኑ አያጠራጥርም:: በርግጥ "ዕጥፍ ቅባት አለኝ"፣ "ቅባት ከእኔ ወደ ሌሎች ይተላለፋል"፣ "ልዩ በሆነው ወርቃማ ቅባት ተቀብቻለሁ"፣ "የእኔ ቅባት ደረጃው ከሌላው ሰው ቅባት ይለያል" ወዘተ የሚሉት ትምህርቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸውን?*

# መቀባት

*በዘመናችን ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ከተረዷቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች መኻል አንዱ ስለ ቅባት ወይም ስለ መቀባት ያለው ትምህርት ነው:: በለስ ሲቀናን "ጌታ እኮ" ነው በማለትና ክብርን ለስኬቱ ጌታ ከመስጠት ፈንታ፣ "ቅባቱ ነው" የሚለው አባባል/አስተሳሰብ ተዘውትሮ የሚደመጥ ጉዳይ ሆኖአል::*

## I. ብሉይ ኪዳን

*በብሉይ ኪዳን አንድ ሰው "ተቀባ" (በዕብራይስጥ "ማሻኽ") ሲባል፣ ከሚከተሉት ትርጉሞች ውስጥ አንዱን ትርጉም ይወክላል፣*

1. *ልተለየ ዐላማ ወይም ተግባር ተሾመ (መዝሙር* 105÷15፤ *ኢሳይያስ* 4÷51):: *ይህ መንፈስ ቅዱስን መቀበልንና ለእግዚአብሔር ለአገልግሎት ብዙ መሆንን ያካትታል* (1*ሳሙኤል* 10÷1:9፤ 16÷13)::
2. *የእግዚአብሔርን ሞገስ ማግኘት (መዝሙር* 23÷5፤ 92÷10)::
3. *የእግዚአብሔር ሥልጣን በተቀባው ሰው ላይ ሆነ ማለት ነው* (2*ነገሥት* 9÷11-13)::

*በአጠቃላይ በብሉይ ኪዳን አንድ ሰው ተቀባ ሲባል ተመረጠ፣ ተሾመ፣ ተለየ (ተቀደሰ) እንዲሁም ለተጠራበት/ለተሾመበት ሥራ ብቃትን/ክህሎትን አገኘ ማለት ነው::*

## II. ሐዲስ ኪዳን

*በአዲስ ኪዳን ግሪክ "ክርዮ" እና "ካሪዝማ" የሚሉት ቃላት "ማሻኽ" የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ተክተው እናገኛቸዋለን:: እንደ ብሉይ ኪዳኑ ሁሉ በአዲስ ኪዳንም "መቀባት" ("ክርዮ" እና "ካሪዝማ") የሚሉት ቃላት የተለያየ ትርጉም ወክለው ጥቅም ላይ ውለዋል::*

1. *ሰውነትን ለማስዋብ ወይም ለመከባከብ ሲባል ሰዎች አካላቸውን የሚቀቡት ቅባት (ማቴዎስ* 6÷17)::
2. *ለእንግዳ ክብር ለማሳየት (ማቴዎስ* 26÷7፤ *ሉቃስ* 7÷38)::
3. *አስክሬንን (ማርቆስ* 14÷8)::
4. *ድውያን ይፈወሱ ዘንድ ጸሎት ለማድረስ (ያዕቆብ* 5÷14)::
5. *መንፈስ ቅዱስ አንድ ሰው ላይ እንዳደረ/እንደ ኖረ ለማሳየት* (1*ዮሐንስ* 2÷20)::
6. *ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለማሳየት (ሉቃስ* 4÷18፤ *ሐዋርያት ሥራ* 4÷26:27፤ 10÷38፤ *ዕብራውያን* 1÷9፤ 2*ቆሮንቶስ* 1÷21):: *ጌታ የተቀባው በእግዚብሔር አብ ነው (ሐዋርያት ሥራ* 10÷38፤ *ሉቃስ* 4÷17-19)::

---

[4] *እነዚህ አባባሎች ምን ትርጉም ይወክላሉ የሚለውን ለመመልከት የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል::*

*ፇ. አማኞች ሁሉ የተቀቡትን መንፈስ ቅዱስ ለማመልከት* (1ዮሐንስ 2÷20:27)።

*በሐዲስ ኪዳን ቅባቱ መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ሲሆን፣ መቀባት ደግሞ ለእግዚአብሔር መለየታቸውንና መንፈስ ቅዱስ እንደሚያድርባቸው ለማመልከት ነው።*

## III. የተሳሳተ ግንዛቤ

*በብሉይ ኪዳን የተወሰኑ አገልጋዮች ለተለየ አገልግሎት ሲለዩና ሲቀቡ እንመለከታለን። በዘመነ ሐዲስ ግን ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ እንደ ተቀባ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በግልጽ ያስተምራሉ* (1ዮሐንስ 2÷20:27)። *"እገሌ የተቀባ ዘማሪ/አገልጋይ ነው" የሚለው አነጋገር፣ ክርስቲያን ሁሉ የተቀባ እስከሆነ ድረስና ክርስቲያን ሆኖ ያልተቀባ እስከ ሌለ ድረስ፣ አነጋገሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። "የእከሊት ድምፅ የተቀባ ነው"፤ "የተቀባ ስብከት ነው"፤ "የተቀባ ትምህርት ነው" ወዘተ የሚሉትም አነጋገሮች ለመጽሐፍ ቅዱስ ባዕድ ናቸው። ቅባት የጸጋ ስጦታ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች እንዳሉ ቢያስተምርም ልዩ ልዩ መቀባቶች/ቅባቶች አሉ ግን አይልም። አማኞች ሁሉ የተቀቡት ቅባት አንድ ዐይነት ቅባት ነው እንዲሁም በተመሳሳይ ቅባት ነው የተቀቡት። መቀባታቸው ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያና የንጉሥ ካህን መሆናቸውን የሚገልጽ ነው። መንፈስ ቅዱስ በውሃ* (ዮሐንስ 7÷37-39)፣ *በእሳት* (ሐዋርያት ሥራ 2÷2)፣ *በርግብ* (ማቴዎስ 3÷16)፣ *ወዘተ እንደ ተመሰለ ሁሉ በቅባትም መመሰሉ እንዲያው ዝም ብሎ ዐይነት ቅባት ነው እንደንል የሚያሰኝን አይደለም። ይልቁንም ባሕርይውንና አገልግሎቱን የሚያመለክት እንጂ። "የተቀባ"* (The Anointed One) *የሚለውም ሙያዊ ቃል በተጸውዖ ስምነት የሚያገለግለው ለክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው* (ሉቃስ 2÷26)።

## IV. የተስያዩ ዐይነት ቅባቶች አሉን?

*መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ቅባት እንጂ፣ የተለያዩ ዐይነት ቅባቶች እንዳሉ አያስተምርም። በቅባት የተመሰለውም መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ለዩ ልዩ አገልግሎት* (1ቆሮንቶስ 12÷5)፣ *ልዩ ልዩ አሠራር* (1ቆሮንቶስ 12÷6)፣ *ልዩ ልዩ ስጦታ አለ* (1ቆሮንቶስ 12÷4) *ይላል እንጂ፣ የተለያዩ ዐይነት ቅባቶች አሉ አይልም—ወርቃማ፣ ብርማ ወዘተ። የተቀባነው ከሌሎች ስለተሻልን፣ የተሻለ ዕውቀት፣ ብርታት ወዘተ ስላለን ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን ብቻ ነው።*

## V. ቅባት ደረጃ አለውን?

*ቅባት ደረጃ አለው የሚለውን ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ለዚህ ትምህርታቸው እንደ ማስደገፊያ አድርገው የሚያቀርቡት የዳዊትን ታሪክ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ዳዊትን በመጀመሪያ የቀባው በቤተ ልሔም በቤተሰቡ ፊት በነቢዩ ሳሙኤል አማካይነት ነበር* (1ሳሙኤል 16÷12-13)። *ለሁለተኛ ጊዜ በይሁዳ ሰዎች ላይ ይነግሥ ዘንድ ዳግም ቀቡት* (2ሳሙኤል 2÷4-7)። *ዳዊት በይሁዳ ሰዎች ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የተቀባው በእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዲሁም በነቢይ ወይም በካህን አማካይነት አይደለም* (2ሳሙኤል 2÷7)። *በሁለተኛ ሳሙኤል* 5÷3 *ዳዊት ዳዊት ከእስራኤል ሽማግሌዎች ጋር ቃል ኪዳን ሲያደርግ በመላው እስራኤል ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የእስራኤል ተወካይ የሆኑት ሽማግሌዎች ሲቀቡት እንመለከታለን። እንደ ሁለተኛው ጊዜ ሁሉ በዚህም ጊዜ እግዚአብሔር እንዲቀቡት ሲያዝ እንዲሁም ተዋቂ ካህን ወይም ነቢይ ሲቀባው አንመለከትም።*

*ከእነዚህ ምንባባ በግልጥ የምንመለከተው እውነት ዳዊት፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝ፣ በዕውቅ የእግዚአብሔር ነቢይ ለንጉሥነት የተቀባው አንድ ጊዜ ብቻ ነው* (1ሳሙኤል 16÷12-13)። *መጀመሪያ ከተቀባበት ጊዜ በኋላ፣ እግዚአብሔር እየደጋገመ ለንጉሥነት ሲቀባው አንመለከትም።* 2ሳሙኤል 2÷4-7 *ላይ የምናነበው በንዳ በቤተሰቦቹ ፊት የተቀባው ዳዊት በይሁዳ ሰዎች ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የተቀባው ንግሥናውን ይፋ ለማድረግ ብቻ ነው።* 2ሳሙኤል 5÷3 *ላይ በእስራኤል ሽማግሌዎች የተካሄደው መቀባት በመላው እስራኤል ላይ ንጉሥ መሆኑን የሚገልጽ ሥርዐት ነው።*

ስለዚህ የዳዊት ታሪክ፣ "መቀባት ደረጃ አለው" ለሚለው ትምህርት መጭራሽ መሠረት ሊሆን አይችልም።

አንድ አማኝ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ማደር በሚጀምርበት ቀን ተቀብቶአል። ስለዚህ ቅባት ደረጃ በደረጃ የምንቀበልበት የልምምድ ሂደት የለም (ሮሜ 8÷9፤ 2ቆሮንቶስ 1÷22-23)።

## VI. ቅባት ይተላለፋልን?

ቅባት እጅ በመጫን፣ የተቀባ ሰው በቆመበት ቦታ በመቆም፣ የተቀባ ሰው የጸለየበትን ጨርቅ በመንካት ወይም ዘይት በመቀባት ወዘተ ይተላለፋል የሚለው ትምህርት ከቃለ እግዚአብሔር የተቀዳ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ሞላባቸው"፣ "ወረደባቸው" ወዘት ይላል እንጂ ትላለፈባቸው አይልም። ቅባት ይተላለፋል የሚሉ ሰዎች ለዚህ ትምህርታቸው እንደ ማስደገፊያ አድርገው የሚጠቅሱት ጥቅስ ዘኍልቍ ምዕራፍ 11 ነው። ክፍሉ ቅባት ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ይተላለፋል የሚል እንዳችም ትምህርት የለውም (በመሠረቱ በክፍሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ እንጂ ቅባት የሚልም ቃል አልተጠቀሰም)። ከሙሴ ወስዶ ለሰባዎቹ የሰጠው ራሱ እግዚአብሔር እንጂ፣ ሙሴ እጁን ስለጫነባቸው፣ ሙሴ በቆመበት ስፍራ ስለቆሙ፣ ሙሴ የጸለየበትን ጨርቅ በእምነት ስለነኩ ወይም በሌላ መንገድ አይደለም። መንፈስ ቅዱስን ለሰዎች መስጠት የሚችለው ልዑል እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ቅባትን ለማስተላለፍ ከላይ የተጠቀስናቸውን መንገዶች ሲጠቀም በፍጹም አናይም። በዚህ ምዕራፍ በቍጥር 26-30 ላይ በኤልዳድና በሞዳድ ላይ፣ "መንፈስ ወረደባቸው" ይላል። ይህም የመንፈስ ቅዱስ ሰጪ ልዑል እግዚአብሔር እንደ ሆነ (የሚወርድ እንደ ሆነ) የሚገልጽ እንጂ፣ የሚተላለፍ እንዳልሆነ ይገልጻል። መንፈስ ቅዱስ አይቈነጠርም፣ አይበዛምም። አንዱ አንደ ነዳጅ ማጠራቀሚያ ዲፖ ሆኖ ከእርሱ እየተቈነጠረ ለሌላው ሰው አይደሰጥም። መንፈስ ቅዱስ ጌታን ባመነ ሰው ሁሉ ውስጥ ያደራል።

## VII. ሁለተ ዕጥፍ ቅባት አለን?

ሁለት ዕጥፍ ቅባት አለ ለሚለው ትምህርት መሠረት ተደርጎ የሚቀርበው የኤልያስንና የኤልሳዕን ታሪክ ነው (2ነገሥት 2)። አስከራሚው ጕዳይ ይህም ክፍል ስለ መቀባት የሚናገረው አንዳችም ነገር ያለመኖሩ ነው። በክፍሉ ውስጥ፣ "ሁለት ዕጥፍ" የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን የበኵር ልጅ የአባቱን ዕጥፍ ንብረት ይወስድ እንደ ነበር የሚገልጽ ነው (ዘዳግም 21÷15-17)። ኤልሳዕ የኤልያስን ዕጥፍ መንፈስ መፈለጉ፣ ኤልያስን በመተካት የነቢያት መሪ ለመሆን መፈለጉን ያሳያል። ኤልሳዕ፣ "ሁለት ዕጥፍ መንፈስ" የሚለው አባባሉ፣ የኤልያስን ቦታ ለመተካት ያለውን መሻት የሚያሳይ እንጂ፣ "ስለ ሁለትዕጥፍ ቅባት" የሚናገር አይደለም።

## VIII. ማጠቃለያ

በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡት የፕሮቴስታንት የተሐድሶ መሪዎች አጥብቀው ከተቃወሟቸው ትምህርቶች መካከል፣ አማኞች ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያለባቸው በካህን በኩል ነው የሚለውን ትምህርት ነበር። ክርስቶስ የቀደደውን/የተረተረውን መጋረጃ መስፋ የለብንም የሚል ነበር። እያንዳንዱ አማኝ የንጉሥ ካህን ነው፤ ስለዚህም ያለማንም ጣልቃ ገብነት ከአምላኩ ጋር በፈለገው ጊዜና በየትኛውም ቦታ መገናገኘት ይችላል።

ዛሬ ይህ የእኛ እንበልጣለን/እንሻላለን ትምህርት መልኩን ቀይሮ በተሐድሶአውያን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መታየቱ የሚያስገርም ነው። "ዕጥፍ ቅባት አለኝ"፣ "ቅባት ከእኔ ወደ ሌሎች ይተላለፋል"፣ "ልዩ በሆነው ወርቃማ ቅባት ተቀብቻለሁ"፣ "የእኔ ቅባት ደረጃው ከሌላው ሰው ቅባት ይለያል" ወዘተ የሚለው አመለካከትና አነጋገር በአማኞች መካከል የተቀባና ያልተቀባ፣ ዕጥፍ ቅባት ያለውን ዕጥፍ ቅባት የሌለው ወርቃማ ቅባት ያለውና ብርማ ቅባት ያለው፣ ወዘተ የሚል ልዩነት የሚያመጣ አንዱን ክርስቲያን ከፍ ሌላውን ክርስቲያን ደግሞ ዝቅ የሚያደርግ ትምህርት ነው።

**እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ኢየሱስ ክርስቶስን አንደ ግል አዳኙ አድርጎ የተቀበለ ማንኛውም ክረስቲያን ተቀብቶአል:: ለመቀባታችን ምክንያቱ ጠንካራ የጸሎት ሰው፣ የቤተ ክረስቲያን መሪ ወይም ሌላው ነገራችን አይደለም:: እግዚአብሔር የቀባን ልጆቹ ስለሆንን ብቻ ነው:: ቅባት እግዚአበሔር በቸርነቱ የሚሰጠን እንጂ፣ ከግለሰቦች የምንቀበለው ነገር አይደለም::**

> "***በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፤ ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው***" (2ቆሮንቶስ 1÷21-22)::
> "***እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል***" (1ዮሐንስ 2÷27)::
> "***እናንተም ከቅዱስ ቅባት ተቀብላችኋል፤ ሁሉንም ታውቃላችሁ***" (1ዮሐንስ 2÷20)::

## ***ይህ ክርስቲያናዊ ትምህርት ነውን?***

ምን አስ ምን አስ ምን አስ፣
ምጻፉ ምን አስ፣
ምን ይሳል ምን ይሳል ምን ይሳል
ምጻፉ ምን ይሳል
        ድል ያንተ ነው አስ፣
        ድል ያንቺ ነው አስ፣
        ድል የእኛው ነው አስ::
ትታመማለህ አሳስም፣
ትደኸያለህ አሳስም፣
ትሸነፋለህ አሳስም፣
ትዋረዳለህ አሳስም::
        ታዲያ ምን አስ
ያልተጻፈ ነገር ለምን ትሳለህ፣
እሱ ያሳለህን ለምን ነኝ ትሳለህ፣
ድልን ታገኛለህ ኢየሱስ ስላለህ፣
ባምላክህ ተራራ ትለመልማለህ::

***ይህ ግጥም "በእምነትህ ላይ እምነት ይኑርህ"፣ አዎንታዊ ነገር ከተናከርክ/ካወጅህ የምትሻውን ነገር ታገኛለህ፣ ስለዚህም ክርስቲያን ሊደኸይ፣ ሊታመም ወዘተ አይችልም የሚለውን የነኬኔት ሃጌንን፣ የኬኔት ኮፒላንድን፣ የቻርልስ ካፕስን ወዘተ የትምህርት አስተሳሰብ ተሳቢ ያደረገ ነው:: ይህ ትምህርት በብርካታ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንት የተወገዘ እኩይ ትምህርት ነው[5]::***

[5] ***ስለዚህ መናፍቃዊ እንቅስቃሴ በስፋት ማወቅ ከፈለጉ፣ ግርማዊ ቡሽ፤ *የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ* እንዲሁም ተሾመ ነጋሽ፤ *እስከ መጣ ድረስ* እንዲሁም የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ *በእምነት መኖር* በሚል ርእስ ያዘጋጇቸውን መጻሕፍት ይመለከቷል::***